Advocates for Youth
Rights. Respect. Responsibility.®

# ለመጠየቅ ምቹ የሆኑ ወላጅ ነዎት?

ሀቆች

እንደ ወላጅ ወይም እንደ ተንከባካቢ ለመጠየቅ ምቹ መሆን በጣም ጠቃሚ ነው። ይህ ምን ማለት ነው? ዐዋቂዎች እንዴት ነው ለመጠየቅ ምቹ የሚሆኑት?

ለመጠየቅ ምቹ መሆን ማለት ወጣቶች እርስዎን ጥያቄ ለመጠየቅ ነፃ እንዲሆኑ ማድረግ ወይም የማያስፈሩ ሆነው እንዲያገኙዎት መሆን ነው። የቁንጅና መስህብን ወይም ጾታ ነክ ጥያቄዎችን (sexuality) በሚመለከት ለመጠየቅ ምቹ ሆኖ መገኘትን ወላጆች ወይም አሳዳ ጊዎች ይፈልጉታል። ነገር ግን አብዛኞዎቹ ይህንን ከባድ ሆኖ ያገኙታል። ዐዋቂዎች በልጅነታቸው ትንሽ መረጃ ብቻ ያገኙ ወይም ደግሞ ምንም ዐይነት መረጃ የሌላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ከፍራቻም ይሁን በማፈር ምክንያት በልጅነት ጊዜ ስለ ግብረ-ሥጋ ግንኙነትን በሚመለ ከት በቤታቸው ስለ አልተወያዩ ይሆናል። ወይም ደግሞ ስለሚከተሉት ነገሮች ይጨነቁ ይሆናል፡:

- ትክክለኛ ቃላትን ወይም መልሶችን ዐለማወቅ፤
- በታናናሾቻቸው ፊት ከዚህ ጉዳይ ውጪ ሆኖ መታየት፤
- በጣም ብዙ ወይም በጣም ትንሽ መረጃ መስጠት፤ ወይም
- ትክክለኛ ባልሆነ ሰዓት መረጃ መስጠት

ለመጠየቅ ምቹ መሆን በጣም ጠቃሚ ነው። የጥናት ውጤት እንደሚያሳየው የቁንጅና መስህብን እና ጾታ-ነክ አደገኛ ባህሪያትን በሚመ ለከት ጥቂት ትክክለኛ መረጃ ብቻ ያላቸው ወጣቶች በርካታ መረጃ ካላቸው ልጆች ይልቅ በለጋ እድሜያቸው ይጀምራሉ። [1,2,3,4,5] በተጨማሪም ከወላጆቻቸው ጋር ወይም ከሌላ የቅርብ ዐዋቂ ሰው ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነትን እና መከላከያን በሚመለከት ውይይት የሚያደርጉ በዐሥራዎቹ የእድሜ ክልል ያሉ ልጆች ከወላጆቻቸው ወይም ከሌሎች ዐዋቂዎች ጋር ውይይት ከማያደርጉት ይልቅ ቶሎ የግ ብረ-ሥጋ ግንኙነት የመጀመራቸው አጋጣሚ/ ወይም መከላከያ የሌለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት የማድረጋቸው ሁኔታ አነሥተኛ እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ።[6,7,8,9] በመጨረሻም ብዙውን ጊዜ ወጣቶች የግብረ ሥጋ፤ ግንኙነቶችን፤ እና ቁንጅናዊ ጤንነትን በሚመለከት ከወላጆቻቸው ጋር መነጋገር እንደሚፈልጉ ይናገራሉ። ይህን ጉዳይ በሚመለከት ወላጆቻቸው ተመራጭ የመረጃ ምንጮች ናቸው።[10,11]

ለመጠየቅ ምቹ መሆን በጣም አስፈላጊ በመሆኑና ከልጆቻቸው ጋር ግብረ ሥጋን የሚመለከቱ ውይይቶችን የመጀመር ችግር ስላለባቸው በርካታ ዐዋቂዎች አዲስ ክህሎቶችን መማርና ቁንጅናዊ መስህብን በሚመለከት ረገድ ውይይት የማድረግ ችሎታቸው እንዲዳብር ይፈል ጋሉ። የሚከተሉት ከጾታ ትምህርት ባለሙያዎች የቀረቡ ጠቃሚ መረጃዎች ናቸው።

## ቁንጅናዊ መስህብን በሚመለከት ከወጣቶች ጋር መነጋገር

1. ትክክለኛ እና መሠረታዊ የሆነ መረጃ ከአስተማማኝ ምንጮች ማግኘት። ቁንጅናዊ መስህብ ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ይልቅ ሰፋ ያለ ርዕስ መሆኑን ማስታወስ። በርግጥ የተፈጥሮ ሣይንስን እና ጾታን ያካትታል። ነገር ግን ስሜትን፤ መቀራረብን፤ መንከባከ ብን፤ መካፈልን፤ መውደድን፤ አመለካከትን፤ ማሽኮርመምን፤ እና ጾታዊ ግንዛቤን እንዲሁም መራባትን እና የግብረ ሥጋ ግንኙ ነትን ሁሉ ያካትታል።

2. ስለሰውነት ክፍሎችና ተግባሮቻቸው ትክክለኛ ቃላትን መማርና መጠቀም። አንዳንድ ቃላትን ያለማፈር የመናገር ችግር ካለብ ዎት በግልዎና እና መስታወት እያዩ ልክ ሌሎች ጾታ-ነክ ያልሆኑ ቃላቶችን የሚጠቀሙትን ያህል ምቾት እስኪሰማዎ ድረስ ይለ ማመዱ። ለምሳሌ “ክንድ” ለማለት የሚቀልዎትን ያህል “የወንድ ብልት” (“penis”) ማለት መቻል አለብዎት።

3. መውደድን እና ግብረ ሥጋን በሚመለከት በራስዎ ስሜቶች እና መመሪያዎች ረገድ ያስቡ። የልጅነት ትዝታዎን፤ የመጀመሪያ ፍቅርዎን፤ መመሪያዎችዎን፤ አሁን ጾታ ነክ ጉዳዮችን በሚመለከት የሚሰማዎትን ስሜት ማለትም የወሊድ መከላከያዎችን፤ የመራባት መብቶችን፤ እንዲሁም የግብረ-ሥጋ ግንኙነት፤ የጾታ እና ጾታዊ ግንዛቤ እኩልነትን ሁሉ ያካትቱ። ከወጣቶች ጋር በአግባቡ ከመወያየትዎ በፊት መጀመሪያ ምን እንደሚሰማዎት ማወቅ አለብዎ።

4. ከልጅዎ ጋር ይነጋገሩ። ከመናገርዎ የበለጠ ያዳምጡ። እርስዎ እና ልጅዎ ግልጽና የሁለትዮሽ ግንኙነት ያላችሁ መሆኑን ያረጋ ግጡ። ይህ ሁኔታ በእርስዎና በልጅዎ መካከል አዎንታዊ (ጤናማ) ግንኙነት ለመፍጠር መሠረት የሚጥል ነው፡ና። እርስ በርስ በመደማመጥ ብቻ ነው መግባባት የሚቻለው። ብዙውን ጊዜ በተለይ ፍቅርን እና ቁንጅናዊ መስህብን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ወጣቶች እና ዐዋቂዎች በተለያየ መልኩ ይመለከቷቸዋል።

5. ለሚከተሉት ሁኔታዎች አይጨነቁ—

- "ከሁኔታው ጋር ስለ መቆየት" (Being "with it.") ያንን ከእኩዮቻቸው ጋር ያደርጉታል። ከእርስዎ የሚፈልጉት ምን እንደሚያምኑ፤ ማን እንደሆኑ እና ምን እንደሚሰማዎት ማወቅ ነው።
- ስለማፈር። ልጆችዎም ያፍራሉ። ያ ችግር የለውም። ምክንያቱም ፍቅር እና የግብረ-ሥጋ ግንኙነትን ጨምሮ ብዙዎቹ የቁንጅናዊዊ መስህብ ሁኔታዎች ከፍተኛ የግል ጉዳዮች ናቸው። ወጣቶች ይህን ይረዳሉ።
- የትኛው ወላጅ ይህንን ጉዳይ መነጋገር እንዳለበት ስለመወሰን። ማንኛውም አፍቃሪ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ለልጁ/ጇ ጠቃሚ ጾታ ነክ ጉዳዮችን ማስተማር ይችላል/ትችላለች።
- አንዳንድ መልሶችን ስለመሳት። አላውቅም ማለት ምንም ማለት አይደለም። መልሱን ለማግኘት ለመሞከር ወይም መልሱን ከልጅዎ ጋር ለማግኘት ለመጣር ይወስኑ። እናም ያድርጉት።

## ከልጆች ጋር መነጋገር

1. አንድ ሰው ጥያቄ ለመጠየቅ ከደረሰ/ች ትክክለኛ መልስ ለመስማት እና ትክክለኛ ቃል (ቃላት) ለማወቅም የደረሰ/ች መሁኑን ያስታውሱ።
2. ልጅዎ እየጠየቀ ያለውን ነገር የተረዱ መሆኑን ያረጋግጡ። እንደገና ይመልከቱ። ለምሳሌ "እየጠየክ/ሽ ያለውን ጥያቄ በትክክል መረዳቴን እርግጠኛ አይደለሁም? እየጠየከኝ/ቅሽኝ ያለው ይህንን ማድረግ ስለመቻሉ ወይም ሰዎች ለምን ይህን እንደሚያደ ርጉ ነው?" ማለት ይችላሉ። የልጁን ጥያቄ የማይመልስ ረጅም ማብራሪያ ውስጥ መግባት የለብዎትም።
3. ጥያቄውን በሚጠየቁበት ጊዜ ወዲያውኑ መልስ መስጠት። ብዙውን ጊዜ ልጅዎን ከማሳፈር ወይም የማስተማሪያ አጋጣሚን ከማባከን ይልቅ የተወሰኑ ዐዋቂዎችን ማሳፈር (ለምሳሌ ሱፐርማርኬት ውስጥ) ይሻላል። በተጨማሪም ልጅዎ በአብዛኛው ወዲያውኑ እና ድምፅዎን ዝቅ አድርገው ቢመልሱ ይመርጣል/ትመርጣለች። በወቅቱ ካልመለሱ ልጅዎ ስለጠየቀ/ች ደስ ያለዎት መሆኑን በመግለጽ ሙሉ ለሙሉ መቼ እንደሚመልሱለት/ላት ጊዜውን ይወስኑ። "ይህንን ስለተየቅህ/ሽ በጣም ደስ ብሎኛል። ስለዚህ ጉዳይ ወደቤት እየተመለስን እንነጋገራለን።"
4. ልጅዎ ሊገባው የሚችልበት ደረጃ ነው ብለው ከሚያስቡት የመረዳት ደረጃ ትንሽ በለጥ አርገው ይመልሱ። ይህም ለሁለት ምክንያት ነው፤ አሱን/አሷን ዝቅ አድርገው እየገመቱ ሊሆን ስለሚችል እና ለወደፊት ጥያቄዎች ክፍተት ስለሚፈጥር ነው። ነገር ግን ከትንሽ ልጅ ጋር እያወሩ መሆኑን አይርሱ። ለምሳሌ በወንዶች እና በሴቶች መካከል ስላለ ልዩነት ሲጠየቅ መጽሐፍ አውጥተው የመራቢያ የሰውነት ክፍሎችን ሥዕል ማሳየት የለብዎትም። ወጣት ልጅ ከዚያ ውጪ በተጨማሪ ምን እንዳለ ማወቅ ይፈልጋል/ትፈልጋለች። ስለዚህ በቀላሉ "ወንድ የወንድ ብልት አለው ሴት ደግሞ የሴት ብልት አላት" ብለው ይመልሱ።
5. ከወጣት ልጆችዎ ጋርም ቢሆን ገደብ ማበጀት እንደሚኖርብዎት ያስታውሱ። የግል ጉዳዮችን ላለመመለስ ይችላሉ። "በአባትህ እና በእኔ መካከል የሚኖር ነገር የግል ጉዳይ ነው። ስለዚህ ጉዳይ ከሌላ ከማንም ሰው ጋር አላወራም" እንዲሁም ልጅዎ ከሚ ጠይቀው/ከምትጠይቀው ጥያቄ አንጻር በእሴቶች እና በመስፈርቶች መካከል ስላሉት ልዩነቶች የተረዳ/ች መሁኑን ያረጋግጡ። ለምሳሌ ልጅ እባላዘሩን በእጁ እየነካካና እያሟሟቀ ጾታዊ ስሜቱን በራሱ ማርካት (masturbate) መጥፎ መሆኑን እና አለ መሆኑን ቢጠይቅ "ማስተርቤት ማድረግ መጥፎ አይደለም ነገር ግን በአደባባይ ማስተርቤት አናደርግም። ያን ማድረግ የግል ባህሪ ነው" ማለት ይችላሉ [እሴቶች ከመስፈርቶች አንጻር]። በተጨማሪም ሌሎች ዐዋቂዎች ተመሳሳይ መለኪያ ቢኖራቸውም የተለየ እሴት ሊኖራቸው እንደሚችል ለልጅዎ ማስገንዘብ ይኖርብዎታል። ማለትም ይህንን ማድረግ ስሕተት ነው ብለው ሊያ ምኑ እና በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን ማድረግ የግል ባህሪ ነው ሊሉ እንደሚችሉ።

## በዐሥራዎቹ የእድሜ ክልል ካሉ ወጣቶች ጋር መነጋገር

1. በዐሥራዎቹ የእድሜ ክልል እያሉ የነበርዎትን ስሜት ያስታውሱ። ወጣትነት አስቸጋሪ ጊዜ እንደሆነ ያስታውሱ። በአንድ ቅጽ በት በዐሥራዎቹ የእድሜ ክልል ያለ ወጣት የተለየ ማንነትን እና ነፃነትን ሊፈልግ እና በሚቀጥለው ቅጽበት ደግሞ በአስቸኳይ የዐዋቂዎችን እርዳታ ሊፈልግ ይችላል።

2. በዐሥራዎቹ የእድሜ ክልል ያሉ ወጣቶች እርስ በርስ መከባበር ያለበት ውይይት እንደሚፈልጉ ያስታውሱ። ማንበብን ያስወ ግዱ። የራስዎን ስሜቶች፤ እሴቶች እና አመለካከቶች ያካፍሉ፤ እንዲሁም እነሱንም ያዳምጡ ስለነሱም ይማሩ። የማንንም ሰው ስሜቶች፤ አመለካከቶች እና እሴቶች ጫና ማድረግ እንደማይቻል ያስታውሱ።

3. ወጣቱ በቁንጅናዊ መስህብ ተሞክሮ ያለው ወይም የሌለው እንዲሁም ዐዋቂ እና ያልበሰለ ብለው አይገምቱ። ወጣቱ የሚለ ውን እና/ወይም የሚጠይቀውን በጥንቃቄ ያዳምጡ። የራስዎን ፍራቻ ወይም ጭንቀቶች ሳይሆን የወጣቱን ትክክለኛ ጥያቄ ይመልሱ።

4. የተለያዩ አማራጮችን ጥቅምና ጉዳት በመመዘን ወጣቱ ያለውን ችሎታ ዝቅ አድርገው አይመልከቱ። ወጣቶች እሴቶች ያሏ ቸው ሲሆን በተለይ ሁሉንም የሚፈልጉትን እውነታ ሲያገኙና ድጋፍ ሰጪ ከሆነ ዐዋቂ ጋር የመወያየት እድል ሲኖራቸው ብስ ለትና ኃላፊነት የተሞላባቸው ውሳኔዎችን የማድረግ ችሎታ አላቸው። ግልጽ እና ትክክለኛ የሆነ መረጃ ሲሰጡ በእርስዎ እም ነት የሚኖረውን/የሚኖራትን ያህል በዐሥራዎቹ የእድሜ ክልል ላላ ልጅዎ የተሳሳተ መረጃ ከሰጡ ለእርስዎ ያለውን/ያላትን አመኔታ ያጣል/ታጣለች። በርግጥ የወጣቱ ውሳኔ እርስዎ ከሚሰጧቸው ውሳኔዎች የተለዩ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ነገር ግን ያ በራሱ ክልል መሄድ ያለበት ጉዳይ ነው።

ለመጠየቅ ምቹ መሆን በሕይወት ሙሉ የሚደረጉ ግንኙነቶች ክፍል (አካል) ነው። ለቅርብ ግንኙነት እና ለቤተሰባዊ ትስስር በር ይከፍ ታል። ለመጀመር መቼም ቢሆን የዘገየ አይሆንም!

## ማጣቀሻ መጻሕፍት

1. Kirby D. *Emerging Answers: Research Findings on Programs to Reduce Teen Pregnancy*. Washington, DC: National Campaign to Prevent Teen Pregnancy, 2001.

2. Baldo M, Aggleton P, Slutkin G. *Does Sex Education Lead to Earlier or Increased Sexual Activity in Youth?* Presentation at the IX International Conference on AIDS, Berlin, 6-10 June, 1993. Geneva: World Health Organization, 1993.

3. UNAIDS. *Impact of HIV and Sexual Health Education on the Sexual Behaviour of Young People: A Review Update*. [UNAIDS Best Practice Collection, Key Material] Geneva: UNAIDS, 1997.

4. Alford S et al. *Science & Success:Sex Education & Other Programs that Work to Prevent Teen Pregnancy, HIV & Sexually Transmitted Infections*. Washington, DC: Advocates for Youth, 2003.

5. Thomas MH. Abstinence-based programs for prevention of adolescent pregnancies: a review. *Journal of Adolescent Health* 2000; 26:5-17.

6. Miller KS et al. Patterns of condom use among adolescents: the impact of mother-adolescent communication. *American Journal of Public Health* 1998; 88:1542-1544.

7. Shoop DM, Davidson PM. AIDS and adolescents: the relation of parent and partner communication to adolescent condom use. *Journal of Adolescence* 1994; 17:137-148.

8. Jemmott LS, Jemmott JB. Family structure, parental strictness, and sexual behavior among inner-city black male adolescents. *Journal of Adolescent Research* 1992; 7:192-207.

9. Rodgers KB. Parenting processes related to sexual risk-taking behaviors of adolescent males and females. *Journal of Marriage and Family* 1999; 61:99-109.

10. Hacker KA et al. Listening to youth: teen perspectives on pregnancy prevention. *Journal of Adolescent Health* 2000; 26:279-288.

11. Kaiser Faimly Foundation, Nickelodeon, and Children Now. *Talking with Kids about Tough Issues: a National Survey of Parents and Kids*. Menlo Park, California: The Foundation, 2001.

በ *Written by* በ *Barbara Huberman, RN, MEd,* እና በ *Sue Alford, MLS* የተደረሰ።
Advocates for Youth © 2005